AMHARIC

**የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ**

**የገንዘብ ድጋፉ ዓላማ ምንድ ነው?**

Port of Seattle **የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍን** ያቋቋመው በፍትሃዊነት ላይ የተመሠረተ ሽርክናን ለማዳበር እና ሀብቶችን እና ድጋፍን በአውሮፕላን ማረፊያው አቅራቢያ ላሉ ማኅበረሰቦች ለማቅረብ ነው። የገንዘብ ድጋፉ በ2019 እና 2023 መካከል 10 ሚሊዮን ዶላር የሚሰጠው ፣ የጩኸት ቅነሳ ሁኔታን ለማቃለል ፣ በእዚህ በዘር እና በባህል በተለያየ ማኅበረሰብ ውስጥ የአካባቢ ጤና እና ዘላቂነትን ለማስገንዘብ ነው።

በማኅበረሰባችን ላይ አስከፊው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፀዕኖ ምላሽ ለመስጠት የ Port Commission **ለደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ** ተጨማሪ ትኩረት እንዲሆን የምጣኔ ሀብት ልማትን አክሏል።
ከሁሉም የዋሽንግተን ቁልፍ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ጋር ባለው ትስስር እና በእኛ ተቋማት ውስጥ ከሚሰሩ ከ 500 በላይ አሠሪዎች ጋር በተገናኘ ፣ ወደቡ የክልሉን መልሶ ማቋቋም ለመምራት እንዲረዳ በተለየ ሁኔታ የተቀመጠ ነው።

**2020: የመጀመሪያ የእርዳታ ዑደታችን**

የደቡባዊ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ በወደቡ ክልላዊ መልሶ ማገገሚያ ስልት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።
በዚህ ዓመት እርዳታውን የምንሰጠው አሁን ባለው የምጣኔ ሀብት ቀውስ በጣም የተጎዱ ማኅበረሰቦችን ለሚያገለግሉ ድርጅቶች ሲሆን ፤ ይህም ከወደብ ጋር የተገናኙ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለተያያዙ ፕሮጀክቶች ፤ የአየር በረራ ሥራን ፣ የባህርን ፣ የግንባታ ንግዶች እና የአካባቢያዊ ሥራ እንዱስትሪዎች ጨምሮ ይሆናል።

ወደቡ ለደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ የመጀመሪያ እርዳታ ዑደት አሁን ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ይገኛል። የማመልከቻው የጊዜ ገደብ እሮብ መስከረም 30 ቀን 2020 ፣ ቀትር 12:00 ሰዓት (ፓሲፊክ ሰዓት) ነው።

- ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ በዚህ ዑደት ውስጥ 1 ሚሊዮን ዶላር የሚገኝ ሲሆን ጥያቄዎች እስከ $100,000 ሊሆኑ ይችላሉ።
- የፕሮጀክቱ ዉጤቶች ከወደብ የተገናኙ እንዱስትሪዎች ዉስጥ የሰው ኃይል ልማት ፣ ስራ ፈጠራ ፕሮግራሞች ወይንም የኢኮኖሚ ማገገሚያ መፍትሔዎች ጋር የተገናኙ መሆን አለባቸው።
- በእነዚህ የመርሐ ግብር ዘርፎች ውስጥ የሚሠሩ የማኅበረሰብ ድርጅቶች ፣ የንግድ ክፍሎች እና ሌሎች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ለማመልከት ብቁ ናቸው።
- ድርጅቶች በአውሮፕላን ማረፊያው አቅራቢያ ያሉ ማኅበረሰቦች ውስጥ ያሉ ፣ በምጣኔ ሀብት ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን እና ታላላቅ ፈታኝ ሁኔታ ያጋጠማቸውን ማኅበረሰቦች የማገልገል ተሞክሮአቸውን ማሳየት አለባቸው።
- ድርጅቶች በጽሑፍ የቀረበ የሀሳብ ጥቆማ ማቅረብ እና ከገምጋሚ ቡድን ጋር የሚደረግ ዉይይት ላይ መሳተፍ አለባቸው ።

**ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

ከወደብ ጋር የሚሰሩት ምን ዓይነት ድርጅቶች ናቸው?

በአሁኑ ጊዜ ፣ በተለያዩ መርሃግብሮች ላይ ያሉ የወደቡ አጋር ድርጅቶች ፤ የሥራ ስልጠና እና ምደባ ፣ ቅድመ-ሙያ ሥልጠና ፣ የሥራ ዕድገት እና ማቆየት ፣ የወጣቶች ስልጠና እና ሥራ ቅጥር ፣ ለአነስተኛ ንግድ የቴክኒክ ድጋፍ ፣ ቱሪዝምን ማስተዋወቅ፣ የአካባቢ ጤንነት እና የህዝብ መሻሻልን ይጨምራል።

የብቁነት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
አመልካቾች ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይም በስሙ የሚያመለክትለት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (fiscal sponsor)ያለው ድርጅት መሆን አለባቸው።

- በስሙ ለሌላ የሚያመለክት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (fiscal sponsor) በመሆን የሚያገለግል ድርጅት ድጋፍ ያደረገለትን ድርጅት ወክሎ ካስገባው ማመልከቻ በተጨማሪ የራሱን ማመልከቻ ማስገባት ይችላል።
- በትብብር ማመልከት ይቻላል ፤ ነገር ግን በትብብር ውስጥ ያለ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ቡድኑን ወክሎ ማመልከቻውን ማስገባት አለበት።

በተጨማሪም ፣ አመልካቾች ለአውሮፕላን ማረፊያው አቅራቢያ ማኅበረሰቦች ውስጥ ፣ በምጣኔ ሀብት ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን እና ታላላቅ ፈታኝ ሁኔታ ያጋጠማቸውን ማኅበረሰቦች ፣ ባለቀለም ሰዎችን (ነጭ ያልሆኑ))፣ የአገሬው ሰዎችን ፣ ስደተኞችን እና መጤዎችን ፣ ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸውን ፣ አባት ጦሮችን፣ አዛውንቶችን ፣ ወጣቶችን ፣ እና/ወይም አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ፣ የማገልገል ተሞክሮአቸውን ማሳየት አለባቸው።

ለማመልከት የበጎ አድራጎት ድርጅት መሆን አለብኝ?
አዎ ፣ ድርጅትዎ ለትርፍ ያልተቋቋመ ሁኔታ ከሌለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በሆነ በስሙ የሚያመለክትለት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (fiscal sponsor) በኩል ማመልከት ይችላሉ።

አንድ ግለሰብ ማመልከት ይችላል?
አይ ፣ አመልካቾች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ፣ በትብብር የሚሰሩ ወይም በስሙ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ያመለከተላቸዉ ድርጅቶች (fiscal-sponsored) መሆን አለባቸው።

በትብብር የሀሳብ ጥቆማ ማቅረብ ይችላል?
አዎ ፣ በትብብር ማመልከት ይቻላል ፤ ነገር ግን በቡድኑ ስም ጥያቄውን የሚያቀርበው ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት መሆን አለበት።

ቢሮአችን ሲያትል ውስጥ ነው ፤ ነገር ግን ቡድኔ የሚያገለግለው ማኅበረሰብ መሠረቱ ቢዩሪየን ነው። ማመልከት እንችላለን?
አዎ ፣ የቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ ጥቆማ የሚያተኩረው በአየር ማረፊያ አቅራቢያ ያሉ ማኅበረሰቦች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ቅድሚያ በመስጠት እስከሆነ ድረስ።

የሀሳብ ጥቆማዬን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተለየ ሌላ ቋንቋ ማስረከብ እችላለሁን?
ሁሉም በጽሁፍ የሚገባ የሀሳብ ጥቆማ ሰነድ በእንግሊዘኛ መሆን አለበት። ሆኖም ከገምጋሚ ቡድን ጋር የሚደረግ ዉይይት ሲያደርጉ በመረጡት ቋንቋ ሊያደርጉት ይችላሉ። አስተርጓሚ ለማቅረብ ደስተኞች ነን።

ከገምጋሚ ቡድን ጋር የሚደረግ ዉይይት ላይ መሳተፍ የግድ አለብኝ?
አዎ። ዉይይቱ ከገንዘብ እርዳታ ገምጋሚ ኮሚቴ ጋር ስለ ፕሮጄክትዎ በአካል እንድነጋገሩ ዕድል ይሰጥዎታል። እነዚህ በአካል ወይንም ከርቀት ሆኖ የሚደረጉ ዉይይቶች የጽሑፍ ማመልከቻን የሚተኩ ሳይሆኑ ከጽሑፍ ማመልከቻ በተጨማሪ የሚደረጉ ናቸዉ። የሚቀርቡት በእንግልዝኛ የሚከሄዱ ሲሆን አስተርጓሚዎች ይቀርባሉ። በዉይይትዎ ላይ አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን የማመልከቻ ቅጽ ላይ ያሳዉቁን። ለግዜ ሰሌዳ አማራጮች እናነጋግርዎታለን።

ከገምጋሚ ቡድን ጋር በማደርገዉ ዉይይት ላይ አስተርጓሚ እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

ከገምጋሚ ቡድን ጋር በሚደረግ ዉይይት ጊዜ አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ በማመልከቻው ቅፅ ላይ ያሳውቁን።

ከአንድ በላይ የሀሳብ ጥቆማ ማስረከብ እችላለሁ?
ለትርፍ ያልተቋቋመው ድርጅት ለሌላ ፕሮጀክት በስሙ የሚያመለክት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (fiscal sponsor) ሆኖ እያገለገለ ካልሆነ በስተቀር ለአንድ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚፈቀደው አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው።

ረቂቅ ሀሳቤ ምን ያህል ረዥም መሆን አለበት?
የትረካው ክፍል ከስድስት (6) ገጾች ያልበለጠ መሆን አለበት፤ ነገር ግን ታሪክዎን ከዛ ባነሱ ገጾች ሊነግሩን ከቻሉ፣ያ መልካም ነው ። እኛ ፍጹም የሆነ ሰዋስው እየፈለግን አይደለም። ብቻ እርስዎ ስለሚያደርጉት ነገር በአጭሩ ዝርዝሩን ይስጡን ። የማመልከቻው ሽፋን ገጽ ፣የፕሮጀክት በጀት እና አባሪዎች በዚህ ስድስት ገጽ ወሰን ውስጥ አይቆጠሩም።

የገንዘብ ድጎማዎች ለአጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ወይም ለፕሮጀክቶች ናቸው?
እርዳታዎች የሚሰጡት ለአጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ወጪ ሳይሆን ከፕሮጀክት ጋር ለተያያዙ ወጪዎች ነው።

ለነባር ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣሉ?
አዎ ነባር ፕሮጀክቶችም ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ናቸው ። ግን የገንዘብ ድጋፉ የሚሸፍነዉ የድጋፉ ኮንትራት ከተፈረመ በኋላ ያሉትን ክንወኔዎችን ብቻ ነዉ።

የእርዳታውን ገንዘብ ከተቀበልን በየ ስንት ጊዜ ሪፖርት ማስገባት አለብን?
የዓመቱ አጋማሽ ሪፖርት እና የመጨረሻ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

የገንዘብ ድጋፉን መቼ መቀበል እችላለሁ?
ሁሉም የእርዳታ ገንዘቦች ተመላሽ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው። ይህም ማለት በመጀመሪያ ወጪዎችዎን መክፈል እና ከዚያ በኋላ ተመላሽ ገንዘብ መጠየቂያዎን ለወደቡ ማስገባት ይኖርብዎታል። የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኞች በየወሩ ያህል መግባት እና እንደደረሱም የሚከፈሉ ናቸው።

የገንዘብ እርዳታው ለሠራተኞች ጊዜ ሊከፍል ይችላል?
አዎ፣የገንዘብ እርዳታው ለሠራተኞች ጊዜ፣ለቀጥታ ወጪዎች ወይም በፕሮጀክቱ ላይ ለሚሠሩ ተቋራጮች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ።